homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
ስልክ ቁ፦ 1300 650 172
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

ለዚህ ቤት ኗሪዎች፣

**በዛሬው ማስታወቂያ ላይ አስፈላጊና ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት**

እየጻፍልንዎት ያለነው ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታላቁ የቤት ግንባታ (Big Housing Build) የለውጥ ሂደት እና ዛሬ ሴፕቴምበር 20 2024 ስለተገለጸው በአካባቢዎ ስላለው የማህበራዊ መኖሪያ ቤት መልሶ ግንባታ ለማሳወቅ ነው።

እንደ የታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) አካል፣ የቪክቶሪያ መንግስት በሜልበርን ዙሪያ ያሉ የቆዩ ሰማይ ጠቀስ የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች መልሶ ለመገንባት ቀጣዩን ትልቅ እርምጃ እየወሰደ ነው።

## ዛሬ የታወጀው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ በሚከተሉት ህንጻዎች ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን ወደ ሌላ ቦታ የመዛወር እቅድ ለማውጣት ውይይቶች በቅርቡ እንደሚጀምሩ እና በፌብሩዋሪ 2026 እንደሚጠናቀቅ አሳውቀናል፦

- 259 Malvern Road, South Yarra
- 139 Highett Street, Richmond
- 111, 119 & 127 Elizabeth Street, Richmond
- 6 & 8 Anderson Court, Richmond
- 1-5, 7 & 9 Williams Court, Richmond.

## ለፍሌሚንግተን እና ሰሜን ሜልቦርን የመዛወሪያ ማብቂያ ቀን ተገለጿል

እንዲሁም በሚከተሉት ህንፃዎች ውስጥ ያሉ በ2023 መገባደጃ ላይ መዛወር የጀመሩትን ነዋሪዎችን ዝውውራቸው በሴፕቴምበር 2025 እንደሚጠናቀቅ አሳውቀናል፦

- 120 Racecourse Road, Flemington
- 12 Holland Court, Flemington
- 33 Alfred Street, North Melbourne

Amharic | አማርኛ

VICTORIA State Government

## ከጁላይ 2026 በፊት የሚጀመር ሌላ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዝውውር የለም

እስከ ጁላይ 2026 ድረስ ተጨማሪ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች ነዋሪዎች ወደ ሌላ ቦታ መዛወር አለባቸው ብለን አንገምትም። አሁኑ ያሉበት ቤት የመዛወሪያ የጊዜ ሰሌዳ የበለጠ ስናውቅ ከእርስዎ ጋር ተመልሰን እንገናኛለን።

## ይህ ለእርስዎ ምን ማለት ነው

ምንም እንኳን ቤትዎ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ አካል ባይሆንም ፕሮግራሙ በሚቀጥልበት ጊዜ በሌሎች ሰፈሮች ላይ ለውጦችን ሊያስተውሉ ይችላሉ።

## ስለ መልሶ ግንባታ ፕሮግራም

የታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) ተጨማሪ እና የተሻሉ ቤቶችን ለመገንባት ቀጣዩን ትልቅ እርምጃ በመውሰድ፣ በሜልበርን ውስጥ ያሉ 44 የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶችን ጡረታ በማውጣት እንደገና ይገነባል።

እነዚህ የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ቤቶች ዘመናዊ የምቾት፣ የተደራሽነት እና የኢነርጂ ቆጣቢነት መስፈርቶችን በሚያሟሉ አዳዲስ ቤቶች ይተካሉ። ይህ መልሶ ግንባታ አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የድሮዎቹ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ልዩ ንድፍ አሁን ነዋሪዎችን ማግኘት የሚገባቸውን መስፈርቶች ለመጠበቅ እና ለወደፊቱ ብዙ ቪክቶሪያውያን ለማኖር አስቸጋሪ ያደርገዋል። እነዚህን ሕንፃዎች መልሶ በመገንባት ነዋሪዎቹ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ እና ለፍላጎታቸው አሁን እና ለወደፊቱ በሚመች ቤት ውስጥ መኖር እንደሚችሉ እያረጋገጥን ነው።

## ቀጣይ መረጃ እንዴት እንደሚያገኙ

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን በቀጥታ ባይመለከትዎትም፣ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ ከመልሶ ግንባታ ፕሮግራሙ ጋር በቀጣይነት ግንኙነት እንዲኖርዎት እናበረታታዎታለን።

ተጨማሪ መረጃ የሚያገኙበትን ድረ-ገጻችን እዚህ bighousingbuild.homes.vic.gov.au ላይ መጎብኘት ይችላሉ። እንዲሁም የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት  መመዝገብ ይችላሉ።

ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካልዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ በኦንላይን፣ በስልክ ሊያነጋግሩን ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የቤቶች ቢሮ መጎብኘት ይችላሉ። የተሻሉ ቤቶችን ለመገንባት በጋራ ስንሰራ ሁሉንም የህዝብ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎችን ለማሳወቅ እና ለመደገፍ ቆርጠን ተነስተናል።

የከበረ ሰላምታ

**Dannii de Kretser**

*ጊዜያዊ ስራ አስኪያጅ፣ ሆምስ ቪክቶሪያ*